# የባህር በር አጀንዳ!

## የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ የኩሻዊያን፣ ወይስ የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ?





**ልደቱ አያሌው**


ጥቅምት 19 2016 ዓ.ም




## ምጥን ሃሳብ

የባህር-በር ኢትዮጵያ ያለአግባብና በግፍ ያጣችው፣ ለወደፊት ህልውናዋ መቀጠልም አብዝቶ የሚያስፈልጋት ታላቅ አገራዊና ስትራቴጂካዊ አጀንዳዋ ነው። ይሁንና አሁን ላይ ከምትገኝበት እጅግ አሳሳቢ የሆነ የህልውና አደጋ አኳያ ቅድሚያ ልትሰጠው የሚገባ አጀንዳ አይደለም። አሁን ላይ ከሁሉም በላይ የሚያስፈልገን እርቅና ሠላም ነው እንጂ ሌላ አውዳሚ ጦርነት አይደለም። የብሔራዊ ደህንነታችን “ቁጥር አንድ ስጋት” ጠቅላይ ሚኒስትሩ ራሳቸው ናቸውና የኢትዮጵያን ህልውና አስጠብቀን ለማስቀጠል ዛሬ ላይ በቀዳሚነት የሚያስፈልገን የባህር-በር ባለቤትነት ሳይሆን የእርሳቸው ከስልጣን መውረድ ነው።






# መግቢያ

በሴራ ፖለቲካ ትንታኔ የሚያምኑ አንዳንድ ሰዎች የወቅቱን የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ እና የአቶ ኢሳያስ ጠብ የማስመሰል አድርገው ያዩታል። በእኔ እይታ ግን ቢያንስ አቶ ኢሳያስን በአስመሳይነት እምብዛም ስለማልጠረጥራቸው ጠቡን የውሸት አድርጌ አላየውም። ቀድሞውንም የሁለቱ መሪዎች ግንኙነት መርህንና የህዝቦችን የጋራ ተጠቃሚነት መሰረት አድርጎ ሳይሆን የጋራ ጠላታችን የሚሉትን ከምድረ-ገጽ የማጥፋት እኩይ ዓላማ ይዞ የተመሰረተ ስለነበር በስሜትና በጥላቻ ህሊናው ላልተጋረደ ሰው ግንኙነቱ ብዙም ዕድሜ እንደማይኖረው ከጅምሩም ግልፅ ነበር። ይህ ጠብ በአግባቡ ካልተያዘና ወደ ጦርነት ከተቀየረ የባሰ አደጋ ሊያስከትል የሚችል ቢሆንም ቢያንስ በተባበሩ ሁለት አምባገነን መሪዎች ከመገዛት ይልቅ በአንድ አምባገነን መሪ መገዛትና አንድን አምባገነን መሪ መታገል ይቀላልና በሁለቱ አምባገነን መሪዎች መጣላት ኢትዮጵያውያንና ኤርትራውያን "እንኳን ደስ አለን" ልንባባል ይገባናል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ለአለፉት 5 ዓመታት ገባ-ወጣ ሲያደርጉት የቆዩትን አንድ የድጋፍ ማሰባሰቢያ የመጫዎቻ ካርድ ሰሞኑን በአደባባይ መዘውታል። ይህ ካርድ ዛሬ ላይ መመዘዙ አገራዊ ፋይዳው አዎንታዊ ይሁንም አሉታዊ ከፖለቲካ የኃይል አሰላለፍ ለውጥ አኳያ ግን የራሱን ለውጥ ይዞ እንደሚመጣ ከወዲሁ እርግጠኛ መሆን ይቻላል። ይህ የኃይል አሰላለፍ መቀያየር ዘላቂ ለውጥ በማምጣት ረገድ ያለው ሚና ውስን ቢሆንም ጠቡ ጦርነትን እስካላስከተለ ድረስ የኢትዮጵያና የኤርትራ ህዝቦች ከአገዛዝ ነጻ ለመውጣት እያደረጉት ያለውን የወቅቱን ትግል በማገዝ ረገድ የማይናቅ ጠቀሜታ ሊኖረው ይችላል።

እንደ አለመታደል ሆኖ ውለታው ሲታወስለት ባይታይም በኢዴፓ መጠን የባህር-በር ጥያቄን ቋሚ አጀንዳው አድርጎ የታገለ ፓርቲ በአገራችን የለም። ኢዴፓ የባህር-በር ጥያቄን ከ23 ዓመት በፊት በፖለቲካ ፕሮግራሙ ቋሚ አጀንዳው አድርጎ ያካተተ፣ ኢትዮጵያ በጦርነት በተሻሩ የቅኝ-ግዛት ውሎች የአልጀርስን ስምምነት እንድትፈርም መደረጓን በመቃወም በመስቀል አደባባይ ታላቅ ህዝባዊ ሰልፍ ያካሄደ፣ የ140 ሺህ ዜጎችን የተቃውሞ ፊርማ አሰባስቦ ለተባበሩት መንግስታትና ለአፍሪካ ህብረት ያስገባና ኢትዮጵያ የባህር-በር የማግኘት መብት እንዳላትም በየመድረኩ ለዓመታት ሲከራከር የኖረ ፓርቲ ነው። ፓርቲው በወቅቱ የብልጽግና አገዛዝ በተለየ ሁኔታ ህልውናውን እንዲያጣና ከአገሪቱ የፖለቲካ ምህዳር እንዲወገድ የተደረገበት አንዱ ምክንያትም የያዛቸውን አገራዊ አጀንዳዎች ለመቀማት ካለ ፍላጎት ነው።

እኔም የኢዴፓ መስራችና አመራር አባል እንደነበረ የፖለቲካ ሰው የአጀንዳው አቀንቃኝ በመሆን የምታወቅ ነኝ። በዚህም ምክንያት በዛሬዎቹ የባህር-በር አጀንዳ አቀንቃኞች ዘንድ ጭምር የጦረኛ አጀንዳ አቀንቃኝ በመባል ለብዙ ዓመታት ስወገዝና ስብጠለጠል ኖሬአለሁ። ይሁንና ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ወደ ስልጣን ከመጡ በኋላ






ስለ ባህር-በር ጥያቄ አውርቼ አላወቅም። ሰሞኑን አጀንዳው በአዲስ መልክ አነጋጋሪ ሆኖ ብቅ ሲልም በጉዳዩ ዙሪያ አስተያየት ላለመስጠት በመወሰን ዝምታን መርጬ ነበር። ዝምታን መምረጤ ግን በአጋጣሚ ሳይሆን በሚከተሉት ምክንያቶች ነው።

<u>አንደኛ፡-</u> አገሪቱ አሁን ላይ ከምትገኝበት ከፍተኛ የህልውና አደጋ አኳያ ከባህር-በር ጥያቄ በላይ ቅድሚያ ትኩረት ልንሰጣቸው የሚገቡ ሌሎች አሳሳቢ አጀንዳዎች አሉብን ብዬ ስለማምን፤

<u>ሁለተኛ፡-</u> ጠቅላይ ሚኒስትሩ አጀንዳውን በአሁኑ ወቅት ይዘው ብቅ ያሉት ለአገሪቱ ብሔራዊ ጥቅም በማሰብ ሳይሆን የራሳቸውን የፖለቲካ ተቀባይነት ለማጠናከር መሆኑን ስለምረዳ ነው።

ከዚህ እምነቴ በተነሳት በአሁኑ ወቅት በባህር-በር ጥያቄ ዙሪያ ትኩረት ሰጥቶ መወያየትና መከራከር በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሴራ ወጥመድ ላይ መውደቅ ነው ብዬ ስለአመንኩ ምንም ዓይነት አስተያየት ላለመስጠት ወስኜ ነበር።

ነገር ግን ከእኔ ፍላጎት በተቃራኒ አጀንዳው ጠቅላይ ሚኒስትሩ በፈለጉት መንገድ የብዙዎች መነጋገሪያ እየሆነ በመምጣቱ ቀደም ሲል ይዤው የነበረውን አቋሜን በመቀየር በጉዳዩ ላይ አስተያየት መስጠትን መርጫለሁ። ለአጀንዳው ትኩረት ባለመስጠት የጠቅላይ ሚኒስትሩን ሴራ ማክሸፍ ቢቻል ኖሮ የበለጠ የተሻለ ይሆን የነበረ ቢሆንም ውይይቱን መግታት እስካልተቻለ ድረስ ግን የውይይቱ ተሳታፊ በመሆን የታሰበውን ሴራ ማጋለጥና መታገል የተሻለ ይሆናል ብዬ አመንኩ።

ስለሆነም በዚህ መጣጥፌ ***"የባህር-በር ጥያቄ የማን ጥያቄ ነው?፤ አጀንዳውን ዛሬ ላይ ማቀንቀንስ ለምን አስፈለገ?፤ አጀንዳው አሁን ላይ በተያዘው መንገድ ከተገፋበትስ በአገሪቱ አጠቃላይ ጥቅምና ህልውና ላይ የሚያስከትለው አንደምታ ምን ሊሆን ይችላል?"*** በሚሉት መሰረታዊ ጥያቄዎች ዙሪያ የግል ዕይታዬን ለማጋራት እሞክራለሁ።

# 1. የወቅቱን የባህር-በር ጥያቄ መደገፍ ይሻላል ወይስ መቃወም?

ይህንን ጥያቄ ለመመለስ ከመሞከራችን በፊት በቅድሚያ "የባህር-በር ጥያቄ የማን አጀንዳ ነው? ወይም የማን ጥያቄና አጀንዳ ሊሆን ይገባል?" የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ መሞከር ተገቢ ይሆናል። እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ ስንሞክርም ቢያንስ የሚከተሉት አመለካከቶች ከአራት የተለያዩ አቅጣጫዎች ሊነሱ እንደሚችሉ መገንዘብ ተገቢ ይሆናል።

**አንደኛ፡-** ጠቅላይ ሚኒስትሩን እስካሁን በአግባቡ ማወቅ የተሳናቸውና አሁንም ድረስ እርሳቸውን አገር-ወዳድ መሪ አድርገው የሚያዩ ዜጎች የወቅቱ የባህር-በር ጥያቄ እየተቀነቀነ ያለው የአገሪቱን ብሔራዊ ጥቅም




ለማስከበር ነው ብለው ሊያምኑና ጠቅላይ ሚኒስትሩን ሊደግፉ ይችላሉ። በፕሪቶሪያው ስምምነት መፈረም ምክንያት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይን አኩርፈው የነበሩ አንዳንድ የኢትዮጵያ ብሔርተኞችም አቋማቸውን ቀይረው የዚህ ጎራ አካል ሊሆኑ ይችላሉ። ከዚህ በተቃራኒ አቶ ኢሳያስን ለኢትዮጵያ በጎ አሳቢ ሰው ናቸው ብለው የማሰብ የአስተሳሰብ መቃወስ ውስጥ ያሉ አንዳንድ ወንድሞቻችንም አቶ ኢሳያስ እንዴት ይከዳሉ ብለው የአጀንዳው ተቃዋሚ ሊሆኑ ይችላሉ።

**ሁለተኛ፡-** ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይንና የሚመሩትና የብልጽግና አገዛዝ ለኦሮሞ ህዝብ ጥቅም መከበር የሚሰራ የኦሮሞ መንግስት ነው ብለው የሚያምኑ አንዳንድ የኦሮሞ ብሔርተኞችና ተከታዮቻቸው እየተቀነቀነ ያለውን የባህር-በር አጀንዳ በተለየ መንገድ ሊያዩት ይችላሉ። አጀንዳውን "በኦሮሙማ የበላይነት የሚመራና የራሱ የባህር-በር ያለው አዲስ የኩሽ አገር የመመስረት ፕሮጀክት" አካል አድርገው በማየት የጠቅላይ ሚነስትሩ አጀንዳ ደጋፊ ሊሆኑ ይችላሉ።

**ሶስተኛ፡-** ከፕሪቶሪያው የሠላም ስምምነት በኋላ የታየው የኃይል አሰላለፍ ለውጥ ትርጉም ባለው መጠን የበለጠ ሊጠናከር ይችላል። ማለትም፤ የትግራይ ኃይሎች ከሁሉም ነገር በላይ ለሻዕቢያ መደምሰስና መጥፋት ቅድሚያ በመስጠት ለጊዜው ከጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ጎን ሊሰለፉ ይችላሉ። በአንጻሩ ደግሞ የአማራ ኃይሎች የተከፋፈለ አቋም የሚይዙበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል። ማለትም፤ አብዛኛዎቹ አሁን ላይ በአገዛዙ እየደረሰባቸው ካለው ጥቃት ራሳቸውን ለመከላከልና የተጀመረውን ጦርነት ለማሸነፍ ሲሉ ከሻዕቢያ ጋር በመቆም የተቃዋሚነት አቋም ሊይዙ፤ ጥቂቶቹ ደግሞ የተለያዩ አካባቢያዊ ጥቅሞችን በማስላት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይን የመደገፍ አቋም ሊይዙ ይችላሉ።

**አራተኛ፡-** ጠቅላይ ሚኒስትሩ ማንኛውንም አጀንዳ የሚያቀነቅኑት ከአገርና ከህዝብ ጥቅም አኳያ ሳይሆን ከራሳቸው የስልጣን የበላይነት ማስጠበቅ አኳያ ነው ብለው የሚያምኑ ዜጎች ከዚህ አቋማቸው በመነሳት የወቅቱን የባህር-በር ጥያቄ ሊቃወሙት ይችላሉ።

ከእነዚህ አራት የአተያይ ፈርጆች አኳያ የወቅቱ የባህር-በር ጥያቄ የራሱ ደጋፊና ተቃዋሚ እንደሚኖረው ግልፅ ነው። በዚህ ውጥንቅጥ በሆነ የኃይል አሰላለፍ ውስጥ ተገቢ አቋም ለመያዝ ስንሞክር በሚከተሉት ሁለት ቁምነገሮች ዙሪያ ከፍተኛ ትኩረትና ጥንቃቄ ልናደርግ ይገባል። በአንድ በኩል አጀንዳው በሃሳብ ደረጃ ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅም ጋር የተያያዘ መሆኑን በማየት ብቻ ያለአግባብ የጠቅላይ ሚኒስትሩ የሴራ ፖለቲካ ደጋፊ በመሆን የጥፋት ተባባሪ እንዳንሆን፤ በሌላ በኩል ደግሞ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይን ለመቃወም ስንል ብቻ አጀንዳውን ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅም






እስከወዲያኛው የሚለያይና የሚጎዳ ስህተት እንዳንፈጽም መጠንቀቅ ይኖርብናል። በዚህ ዓይነቱ የልዩነት ጠገግ ውስጥ ሚዛን የጠበቀ አቋም ይኖረን ዘንድም በሚከተሉት ሦስት መሰረታዊ ጥያቄዎች ዙሪያ ተገቢ ግንዛቤ ሊኖረን ይገባል።

## 1.1. የወቅቱ የባህር-በር ጥያቄ የአገርና የህዝብ ነው?

ኢትዮጵያ ለብዙ ዘመናት በባለቤትነት ይዛው የኖረችውን የባህር-በሯን ለማጣት የተገደደችው በተለያዩ ወቅቶች የተለያዩ መሪዎቿ በሰሯቸው ስህተቶች ነው። በቅድሚያ ዳግማዊ አፄ ሚኒሊክ በአቅም ማነስ ምክንያት የአገሪቱን የባህር-በር ለውጭ ወራሪ ኃይል አሳልፈው በመስጠታቸው፤ ከዚያም አፄ ኃይለስላሴና ኮሎኔል መንግስቱ ኃይለማሪያም አርቆ አሳቢ መሆን ባለመቻላቸውና በጥንቃቄ ጉድለት ምክንያት አገሪቱን በሂደት የባህር-በር የሚያሳጣ ስህተት በየዘመናቸው በመፈጸማቸው፤ በመጨረሻም ኢህአዴግ ለአገሪቱ ብሔራዊ ጥቅም መከበር ደንታ ቢስ በመሆኑ 1983 ዓ. ም ላይ ያለምንም ቅድመ-ሁኔታና ድርድር ለኤርትራ ነፃ አገርነት እውቅና በመስጠትና ኋላም ላይ በጦርነት የተሻሩ የቅኝ-ግዛት ውሎችን መሰረት ያደረገውን የአልጀርስ ስምምነት በመፈረም ኢትዮጵያን የባህር-በር በማሳጣት ረገድ ታሪክ ይቅር የማይለው ተደጋጋሚ ስህተት ፈጽሟል።

በእነዚህ ተደጋጋሚ የመሪዎች ስህተትና ጥፋት ምክንያት ኢትዮጵያ የባህር-በር የማግኘት እድሏ የበለጠ አስቸጋሪና ውስብስብ እየሆነ መምጣቱን መካድ አይቻልም። ይሁንና ኢትዮጵያ የባህር-በሯን ያጣችው ያለአግባብና በግፍ ጥቅሟን በሚፃረር አስገዳጅ ሁኔታ በመሆኑ፣ የአንድ አገር ህዝብና ትውልድም ብሔራዊ ጥቅሙን በማስከበር ረገድ በቀላሉ ተስፋ መቁረጥ ስለማይገባው የአገሪቱ የባህር-በር ጥያቄ የህዝብና የትውልድ አጀንዳ ሆኖ ዛሬም ሆነ ወደ ፊት መቀጠል ያለበት ነው። “የባህር-በር ባለቤት ለመሆን የምንችለው መቼ፣ ከየት እና እንዴት ነው?” በሚሉት ጥያቄዎች ዙሪያ ልዩነት ሊኖረን የሚችል መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ቀጣይነት ያለው ጠንካራ ትግል ማድረግ ከቻልን ግን የባህር-በር እንደገና የማግኘት እድል እንደሚኖረን ጠንካራ እምነት ሊኖረን ይገባል። በቂ ጥናትና ዝግጅት አድርገን፣ የተለያዩ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የዲፕሎማሲና የህግ አማራጮችን ይዘን ጠንካራ ትግል ማካሄድ እስከቻልን ድረስ ለዘላቂ ህልውናችን ወሳኝ ሚና ያለውን የባህር-በር ጥያቄ ልናሳካው እንደምንችል በቅድሚያ በራስ መተማመን መፍጠር አለብን። የቤት ስራችንን በብስለትና በስክነት መስራት እስከቻልን ድረስም ለውጤት የመብቃት ዕድል እንዳለን አፄ ኃይለስላሴና አቶ አክሊሉ ኃብተወልድ ለ60 ዓመታት ያህል ያጣነውን የባህር-በር እንደገና ለማግኘት ያደረጉት ትግልና ያሳኩት ውጤት ጥሩ ምሳሌና አርዓያ ሆኖ ሊያስተምረን ይችላል።

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ለአለፉት 5 ዓመታት በተደጋጋሚ ሲሆን እንዳየነው ከአገሪቱ ብሔራዊ ጥቅም በላይ ለራሳቸው የስልጣን የበላይነት ቀናዒ የሆኑት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ እንዲህ ዓይነቱን ታላቅ አገራዊ ጥቅም በብቃት የማሳካት ፍላጎትና አቅም ስለማይኖራቸው፤ ከሁሉም በላይ አገራችን በአሁኑ ወቅት ከምትገኝበት የፖለቲካ ቀውስና የህልውና ፈተና አኳያ የባህር-በር ጥያቄን ቀዳሚ የአደባባይ አጀንዳ አድርጎ




ማቀንቀን ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባና በተገቢው ጊዜ የቀረበ ጥያቄ ነው የሚል እምነት የለኝም።

## 1.2. የወቅቱ የባህር-በር ጥያቄ የኩሻዊያን ነው?

በአገራችን የብሔርተኝነት የፖለቲካ እንቅስቃሴ ከጊዜ ወደ ጊዜ ከመለዘብ ይልቅ የበለጠ እየተጠናከረ በመምጣቱ ምክንያት የኢትዮጵያውያን የጋራ ብሔራዊ ጥቅም ባለቤትና ተገቢ ትኩረት እያጣ መጥቷል። በታሪካችን አይተነው በማናውቀው መጠን በስልጣን ላይ የሚገኘው የብልጽግና አገዛዝ ከአገሪቱ ደህንነት በላይ የራሱን የፖለቲካና የስልጣን ጥቅም በማስቀደም የውጭ ኃይሎችን ራሱ በመጋበዝ ጭምር የአገሪቱን ሉዓላዊነት እና ዳር-ድንበር በጠራራ ፀሐይ ሲያስደፍር ታይቷል። የብልጽግናው አገዛዝ የኢትዮጵያ መንግሥት መሆኑን በመካድም በኦሮሞ ህዝብ ትግል ብቻ ለስልጣን የበቃ፤ ለኦሮሞ ህዝብ ጥቅም መከበር በልዩ ትኩረት እየሰራ የሚገኝ የኦሮሞ ተረኛ መንግሥት እንደሆነ አድርጎ ራሱን ሲገልጽ በተደጋጋሚ ታይቷል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ወደ ስልጣን ከመጡና በገዢው ፓርቲ ውስጥ የህወሃት የበላይነት በኦህዴድ የበላይነት ከተተካ በኋላ በኦሮሞ ብሔርተኛ ኃይሎች ዙሪያ ሁለት ፅንሰ-ሃሳቦች ተደጋግመው ሲነሱ ይደመጣል። እነርሱም "ኦሮሙማ እና የኩሽ ህዝቦች አጋርነት" የሚሉ ናቸው።

እነዚህን ፅንሰ-ሃሳቦች በተመለከተ በድርጅት ደረጃ የባለቤትነት ኃላፊነት ወስዶ ተገቢ ትንታኔ የሚያቀርብ አካል ባይኖርም ፅንሰ-ሃሳቦቹ በኦሮሞ ብሔርተኞች የሃሳብ ልውውጥ መድረኮች በጣም ጎልተው የሚሰሙ ጉዳዮች ሆነዋል። ብዙውን ጊዜ በበቂ መጠን ያልታሰበበትና ያልታሸ አጀንዳ ይዘው የሚቀርቡ አክራሪ የኦሮሞ ብሔርተኞች የያዙትን አጀንዳ የሚሞግት ትችት ሲቀርብባቸው ያለአግባብ የሚወራጩና ትችቱን ሁሉ "የኦሮሞ ጠልነት" አድርገው የማቅረብ አባዜ የተጠናወታቸው ቢሆንም ይህ ጉዳይ ከወቅቱ የባህር-በር ጥያቄ ጋር በተያያዘ ተንቆ ሊታለፍ የማይገባውና ተገቢ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ አንድ የዕይታ ገጽታ ነው።

ቀደም ሲል በኦሮሞ ብሔርተኞች ዘንድ በስፋት ይቀነቀን የነበረው የኦሮሚያ የነጻነት ጥያቄ በሂደት በኦሮሙማ የበላይነት ወደሚመራ "የኩሽ አገረ መንግሥት" ጥያቄነት እያደገ ወይም እየተለወጠ የመምጣት አዝማሚያ እያሳየ ነው። በብሔር ደረጃ ይገለፅ የነበረውን የፖለቲካ ልዩነትና ቅራኔ በሂደት በሴማዊና ኩሻዊ ልዩነትና ቅራኔ የማቅረብ አዲስ ርዕዮትና እንቅስቃሴ ተጀምሯል። የዚህ የኩሽ አገር ምስረታ እንቅስቃሴ አድማስም በኢትዮጵያ ማዕቀፍ ብቻ የሚወሰን ሳይሆን በምስራቅ አፍሪካ ደረጃ የሚታይ እንደሆነ በተደጋጋሚ ሲገለጽ ታይቷል።

ለምሳሌ፡- "ኦሮሞ በምስራቅ አፍሪካ ትልቁ ብሔር ነው"፤ "የኛ ዓላማ ከኢትዮጵያ አልፎ ምስራቅ አፍሪካን አንድ ማድረግ ነው"፤ "ኢሬቻን በሚቀጥለው ዓመት ቀይ-ባህር ላይ እናከብራለን" ወዘተ የሚሉ ውስጠ-ወይራ ንግግሮችን ከማድረግም አልፎ አንዳንዶቹ የኦሮሞ ብሔርተኞች "ዓላማችን አቢሲኒያዎች የሌሉበትና ሌሎች ብሔር-




ብሔረሰቦችን ያካተተ ነፃ አገር ማቋቋም ነው” በማለት በድፍረት ሲናገሩ በመስማታችን ጉዳዩ ምንያህል ውስጥ ውስጡን እየተብላላና እየተንተከተከ እንደሆነ ማሳያ ነው።

ከፍ ሲል ለመግለፅ እንደሞከርኩት በድርጅት ደረጃ ኃላፊነት የወሰደ አካል ባይኖርም አፋርንና የተወሰኑ የሰሜን ሶማሊያ አካባቢዎችን አካቶ እስከ ቀይ-ባህርና ህንድ-ውቅያኖስ ድረስ የሚዘልቅ አዲስ “የኦሮሙማ” ካርታ ሲያሰራጩም ታይቷል። ስለሆነም የወቅቱን የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ “ድንበራችን ቀይ-ባህር ነው” የሚል አጀንዳ ከጥርጣሬም ባለፈ መጠን ከዚህ የኩሻዊ የአገረ-መንግሥት ምስረታ ፍላጎት ጋርም አያይዞ ማጤን ተገቢ ይሆናል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ በዓላማ ደረጃ ከራሳቸው የስልጣን የበላይነትና ቀጣይት ባለፈ የኢትዮጵያም ሆነ የኦሮሞ ብሔርተኝነት አጀንዳ አራማጅ ናቸው የሚል እምነት በእኔ በኩል የለኝም። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ለፖለቲካ ስልጣናቸው የሚጠቅም መስሎ እስከታያቸው ድረስ ግን ጠቅላይ ሚኒስትሩ በማንኛውም ጊዜና ሁኔታ ሊያነሱትም ሆነ ሊጥሉት የማይችሉት የትኛውም ዓይነት አጀንዳ አይኖርም። ‘እያደናገሩ ማሳመን’ን ቋሚ የአገዛዝ ስልታቸው አድርገው የሚጠቀሙት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ዛሬ ላይ ስለ ባህር-በር አጀንዳ ትንታኔ እየሰጡ ያሉት ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅም ጋር አያይዘው እንደሆነ እያየን ነው። ይሁንና ከፕሪቶሪያው የሠላም ስምምነት በኋላ ማህበራዊ መሰረታቸውን ከኢትዮጵያና ከአማራ ብሔርተኞች ወደ ኦሮሞ ብሔርተኞች ሲያሸጋግሩ የታዩት ጠቅላይ ሚኒስትሩ በይፋ ሊናገሩት ባይችሉም ከኦሮሞ ብሔርተኞች ጋር በሚኖራቸው የውስጥ ለውስጥ ወይም መደበኛ ያልሆነ ግንኙነት ግን የወቅቱን የባህር-በር ጥያቄ ከኦሮሞ ብሔርተኞች ጥያቄና ፍላጎት ጋር አያይዘው ሊጠቀሙበት እንደሚችሉ መገመት ስህተት አይሆንም።

እንኳንስ ከኢትዮጵያ ብሔርተኞች ጋር ሆድና ጀርባ በሆኑበትና ከአማራ ህዝብ ጋር የለየለት ጦርነት ውስጥ በገቡበት በአሁኑ ወቅት፣ በኢትዮጵያዊ ሙሴነት ይወደሱ በነበረበት ወቅትም ከኦሮሞ ብሔርተኞች ጋር በኦሮምኛ ቋንቋ በሚያደርጓቸው ውይይቶች ራሳቸውን የኦሮሞ ብሔርተኝነት ቻምፒዮን አድርገው ያቀርቡ እንደነበር እናውቃለን። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ “የአፄ ዮሃንስን ልጆች ከገንዘብ፣ የአፄ ሚኒሊክን ልጆች ከስልጣን ነጥያቸዋለሁ፤ አማራ ከእንግዲህ በሚሊዮን ዓመታት ወደ ስልጣን ሊመለስ አይችልም፤ አቢሲኒያዎችን እርስ በርስ እያዋጋሁ ከማዳከም በላይ ለኦሮሞ ህዝብ ምን ውለታ እንድሰራ ትጠብቃላችሁ?” በማለት እንደሚናገሩ በየጊዜው ሾልከው ከሚወጡ ሚስጥሮች የምንሰማው ያለምክንያት ሳይሆን የኦሮሞ ብሔርተኞች አጀንዳን እንደ አንድ ዋና የስልጣን ማስጠበቂያ የመጫወቻ ካርድ አድርገው የሚጠቀሙበት ስለሆነ ነው።

ከዚህ አኳያ ጠቅላይ ሚኒስትሩ የወቅቱን የባህር-በር አጀንዳ ከኦሮሞ ብሔርተኞች ጥያቄና ፍላጎት ጋራ በማያያዝ ውስጥ ውስጡን በኦሮሞ ብሔርተኞች ዘንድ እንዲኖራቸው የሚፈልጉትን ማህበራዊ መሰረት ሊያጠናክሩበት እንደሚሞክሩ መገመት ከባድ አይሆንም። ይሁንና ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ እንዲህ ዓይነቱን አቋም




የሚራምዱት እንደተለመደው ለስልጣናቸው የበላይነት መራዘም ሲሉ እንጂ ለኦሮሞ ህዝብ ጥቅምና ፍላጎት ተቆርቋሪ በመሆን አይደለም። ከወሎ እስከ ቀይ-ባህርና ህንድ-ውቅያኖስ የተንሰራፋ የኩሽ አገረ-መንግሥት የማቋቋሙ ፍላጎትም እንደተለመደው የጥቂት ፅንፈኛ የኦሮሞ ብሔርተኞች የቅዠት አጀንዳ እንጂ የኦሮሞ ህዝብ አጀንዳና ፍላጎት እንዳልሆነ ከልብ መገንዘብ ያስፈልጋል።

## 1.3. የወቅቱ የባህር-በር አጀንዳ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ነው?

በመግቢያዬ ላይ ለመግለጽ እንደሞከርኩት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ወደ ስልጣን የመጡት የተለያዩ የድጋፍ ማሰባሰቢያ ካርዶችን በሴራ ኪሳቸው አጭቀው ነው። በእኔ በኩል በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይና በአቶ ኢሳያስ የተጀመረው መርህ-የለሽ ግንኙነት በቀላሉ ተሰባሪ እንደሆነ፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከያዟቸው የድጋፍ ማሰባሰቢያ ካርዶች ውስጥም እንዱና ዋናው "ወደ ቀይ-ባህር እንዘምታለን" የሚል እንደሚሆን ቀደም ሲል ደጋግሜ ስናገር ነበር። በዚህም ምክንያት አሁን ላይ ጠቅላይ ሚኒስትሩ የባህር-በር አጀንዳን ይዘው ብቅ ማለታቸው የፈጠረብኝ ግርምት የለም። ይልቁንም በእኔ ላይ ግርምት የፈጠረብኝ ከ5 ዓመታት ከበቂ በላይ የሆነ ልምድ በኋላ የጠቅላይ ሚኒስትሩን "እያደናገሩ የማሳመን" የአገዛዝ ስልት በውል ያልተገነዘቡና አገርን የሚጠቅም አጀንዳ መጣልን ብለው በማሰብ አገዛዙን ለመደገፍ የሚዳዳቸው በቁጥር ቀላል የማይባሉ የዋህ ዜጎችን ዛሬም ላይ ማየቴ ነው።

እኔ በአገራችን ፖለቲካ በምክንያት የመደገፍና በምክንያት የመቃወም ባህል እንዲዳብር የአርዓያነት ሚና ለመጫወት የምሞክር ሰው ነኝ። "አንድን በስልጣን ላይ ያለ አገዛዝ የቱንም ያህል የምንጠላውና የምንቃወመው ቢሆንም አገዛዙ ሆን ብሎም ይሁን በአጋጣሚ አገርን የሚጠቅም አጀንዳ ይዞ ከመጣ (በዚያ አጀንዳ ዙሪያ) ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ልንደግፈው ይገባል" የሚል አመለካከት አለኝ። ከዚህ አመለካከቴ ጋር በተያያዘ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሁን ላይ እያቀነቀኑት ያለው የባህር-በር አጀንዳ ለራሳቸው የስልጣን ጥቅም ብለው አምጥተውትም ቢሆንና ነገር ግን እግረ-መንገዱን አገርን የሚጠቅም ትሩፋት ቢኖረው ኖሮ አጀንዳውን ያለምንም ማቅማማት በደገፍኩት ነበር።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ዛሬ ላይ ይዘውት የመጡትን የባህር-በር አጀንዳ የምቃወመው - የሰውየው የፖለቲካ ተቃዋሚ ስለሆንኩ፣ አቶ ኢሳያስ ይጎዳሉ ወይም ክህደት ተፈጽሞባቸዋል ብዬ ስለማስብ፣ ኢትዮጵያ የባህር-በር ጥያቄ የማቅረብ መብት የላትም ብዬ ወይም የባህር-በር ለወደፊት ህልውናዋ አያስፈልጋትም ብዬ ስለማምን አይደለም። ይልቁንም ጉዳዩን የምቃወመው አጀንዳው በአሁኑ ወቅት እንዲቀርብ የተፈለገው የአገሪቱን ብሔራዊ ጥቅም ለማስከበር ተብሎ ሳይሆን ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ስልጣን ማጠናከሪያ ተብሎ መሆኑን ስለምረዳ፤ ከዚህ በተጨማሪም አጀንዳው በተገቢ ጊዜና በጥናት በተደገፈ ዝግጅት የቀረበ ስላልሆነና ውጤታማ የመሆን ዕድል ስሌለው፤ ይልቁንም የአገሪቱን ወቅታዊ ችግሮች በማባባስ ረገድ የበለጠ ጉዳት ያስከትላል የሚል






እምነት ስላለኝ ነው። ይህንን ለማለት ያበቁኝን ምክንያቶችም ከዚህ እንደሚከተለው ለማሳየት እሞክራለሁ።

## 2. የወቅቱ የባህር-በር ጥያቄ ወቅቱን ያልጠበቀና በአቀራረብ ደክመቶች የተሞላ ነው።

ለአለፉት 5 ዓመታት ከበቂ በላይ ደጋግመን እንዳየነው ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከፍተኛ የሚባሉ አገራዊ ውሳኔዎችን ጭምር የሚወስኑት የመንግሥትንም ሆነ የፓርቲያቸውን መዋቅር ሳያማክሩ ነው። የውሳኔአቸውን ፋይዳ በዋናነት የሚመዝኑትም ከአገሪቱ ጥቅምና ፍላጎት አንጻር ሳይሆን ከራሳቸው የስልጣን የበላይነትና ቀጣይነት አኳያ ብቻ ነው። የወቅቱን የባህር-በር ጥያቄ በአደባባይ የማወጅ ውሳኔ የተላለፈውም በተመሳሳይ መንገድ ነው። ጥያቄው እየቀረበ ያለው በበቂ ጥናት፣ ዝግጅትና መዋቅራዊ ድጋፍ ሳይታገዝ ብቻ ሳይሆን ከዓለም-አቀፍ ህግና ከዲፕሎማሲ ሳይንስ አቀራረብ አኳያም ምንም ዓይነት ምክክር ሳይደረግበት ነው። ይህንን ለማለት የሚያስደፍሩ ከበቂ በላይ የሆኑ ማሳያዎች አሉ።

<u>**አንደኛ፡-**</u> ከጊዜ አኳያ ጥያቄው በተገቢ ወቅት ላይ የቀረበ አይደለም። አገሪቱ ህልውናዋን በሚፈታተን የእርስ-በርስ ጦርነት ውስጥ ባለችበት፤ ኢኮኖሚዋ በጦርነት ተንኮታኩቶ የውጪ ብድርና እርዳታ ከመቼውም ጊዜ በላይ ፈላጊ በሆነችበት፤ የአገሪቱ መንግሥት በከፍተኛ ዓለም-አቀፋዊ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ወንጀሎች ፈጻሚነት እየተፈረጀ በሚገኝበት፤ የብልጽግና መንግሥት ከኤርትራ መንግሥት ጋር አዲስ ቅራኔና ውዝግብ ውስጥ በገባበት፤ በአጠቃላይም አገሪቱ ትበታተናለች ተብሎ በተሰጋበትና ጎረቤት አገሮችም ሆኑ ዓለም-አቀፉ ማህበረሰብ ኢትዮጵያን እንደ ከፍተኛ የስጋት ምንጭ እያያት ባለበት በአሁኑ ወቅት እንዲህ ዓይነት ከባድና አወዛጋቢ አጀንዳ ይዞ መምጣት ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ የሚያመዝን ነው። አጀንዳው በአሁኑ ወቅት በአደባባይ መቀንቀኑ ውስጣዊ የፖለቲካ ችግራችንንም ሆነ በዲፕሎማሲ ረገድ ያለብንን ውጫዊ ችግር የበለጠ የሚያባብስና የሚያወሳስብ ይሆናል።

<u>**ሁለተኛ፡-**</u> ከአቀራረብም አኳያ እየቀረበ ያለው የባህር-በር ጥያቄ በብዙ ድክመቶች የተሞላ ነው። ኢትዮጵያ ካለፈችበት የታሪክ ውጣ-ውረድ፣ አሁን ላይ ከምትገኝበት ውስጣዊና ውጫዊ ውጥረት አኳያ የባህር-በር ጥያቄን ማራመድ ያለባት በከፍተኛ ዝግጅትና ጥንቃቄ ሊሆን ይገባዋል። እንኳንስ በአገርና በመንግሥት ደረጃ፣ በተቃዋሚ ፓርቲ ደረጃም ኢዴፓ የባህር-በር ጥያቄን ከ23 ዓመታት በፊት አጀንዳው አድርጎ ሲያቀነቅን የነበረው በጥናት ላይ በተደገፈ ከፍተኛ ጥንቃቄ ነበር። ለምሳሌ ኢዴፓ የባህር በር ጥያቄን አስመልክቶ መግለጫዎች ሲሰጥና ሰነዶችን ሲያቀርብ ጥያቄውን በተለየ ሁኔታ ከወደብ ወይም ከአሰብ ጋር አያይዞ አቅርቦ አያውቅም። የባህር-በር ጥያቄውን ከየትኛው አገር ወይም ውቅያኖስ ለማግኘት እንደሚፈልግም በዝርዝር ካለመግለጹም ባሻገር ጥያቄውን ለማሳካትም የኃይል አማራጭን የመፍትሄው አካል አድርጎ አቅርቦ አያውቅም።






ሰሞኑን ጥያቄውን ሲያቀርቡ በሰማናቸው ዝርዝር ጉዳዮች ላይ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከግል ግንዛቤአቸውና ከፖለቲካ ስልጣን አጀንዳቸው ባለፈ ለአጀንዳው የሚመጥን በቂ ዝግጅት ያላደረጉ መሆኑን በግልፅ የሚያሳዩ ናቸው። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ የባህር-በርና የወደብ ጥያቄን በአግባቡ ለይተው ለማየት ሲቸገሩ መታየታቸው፣ የባህር-በርን ያህል ትልቅ ጉዳይ እንደቀላል ነገር በንግድ ድርጅት የአክሲዮን ድርሻ ለመለወጥ ሲመኙ መታየታቸው፣ ከየትኛው አገርና ውቅያኖስ የባህር-በር ማግኘት እንደሚፈልጉም "ድንበራችን ቀይ-ባህር ነው" በማለት ጭምር በድፍረት ሲናገሩ መደመጣቸው፣ ስለ ባህር-በር ጥቅም ለማስረዳትም በሰው አካል ውስጥ የሚኖርን የውሃ መጠን ማነፃፀሪያ አድርገው ማቅረባቸው፣ "ማንኛውንም መስዋዕትነት በመክፈል" የሚል አባባል በመጠቀምም የባህር-በርን ለማግኘት የኃይል አማራጭን ጭምር ሊጠቀሙ እንደሚችሉ በአደባባይ ሲናገሩ መደመጣቸው፤ በአጠቃላይም ጉዳዩን በህጋዊና መዋቅራዊ ድጋፍ ታግዘውና የሰከነ የዲፕሎማሲ አቀራረብ ተጠቅመው ሳይሆን በመግለጫና በመገናኛ ብዙሃን የፕሮፓጋንዳ ዘመቻነት ሲያቀርቡት ማየታችን አጀንዳው እየቀረበ ያለው ያለበቂ ጥናትና ዝግጅት መሆኑን በግልፅ የሚያሳይ ነው።

ጥያቄው በአደባባይ ከታወጀ በኋላ ጉረቤት አገሮቻችን በፍጥነት የተቃውሞና የስጋት መግለጫ ሲያወጡ ያየናቸው ያለምክንያት ሳይሆን ቢያንስ እነሱን እንኳን የማግባባት የዲፕሎማሲ ስራ አስቀድሞ ያልተሰራ በመሆኑ ነው። በአሁኑ ወቅት 'ከአቶ ኢሳያስ ጋርም ቢሆን ወደ ጦርነት መግባት አስፈላጊ አይደለም' ብዬ በእኔ በኩል የማምን ብሆንም፣ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ብልህ መሆን ባይችሉም እንኳ ብልጥ ለመሆን ቢሞክሩ ኖሮ ከአቶ ኢሳያስ ጋርም ወደ ጦርነት መግባት ያለባቸው በባህር-በር ጥያቄ ምክንያት ሳይሆን ሻዕቢያ በኃይል የያዛቸውን የኢትዮጵያን ግዛቶች ምክንያት በማድረግ ቢሆን የተሻለ ነበር።

"ቀይ-ባህር ድንበራችን ነው" የሚል መፈክር እያሰሙ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ጦርነት ለማወጅ መሞከር በወራሪነት የሚያስፈርጅና ከፍተኛ ዓለም-አቀፋዊ ጫና የሚያስከትል ነው። ከባህር-በር ጋር ተያይዞ የሚነሳ ጦርነት ሊካሄድ የሚችለው ከሻዕቢያ ጋር ብቻ ሳይሆን ወንድም ከሆነው የኤርትራ ህዝብ ጋር ስለሚሆንም ጦርነቱ ፍትሃዊ አይሆንም ብቻ ሳይሆን በቀላሉ ተገብቶ ሊወጣበት የሚቻል አይሆንም። የጦርነቱ ምክንያትም ቀይ-ባህር ከሆነም አብዛኛው ኤርትራዊ የአቶ ኢሳያስ ደጋፊ የመሆን አቋም ሊይዝና እድሜአቸውን የበለጠ የማራዘም አደጋ ሊፈጥር ይችላል።

በአጠቃላይ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ የባህር-በር ጥያቄን በአደባባይ ባወጁ ማግስት "የኤርትራ መንግሥት ግዛቴን አልለቅልኝ አለ" ብለው ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት ደብዳቤ መጻፋቸው የሚያሳየን ሰውየው ምን ያህል የዲፕሎማሲ "ሀ...ሁ..."ን ያልተገነዘቡ የአገር መሪ መሆናቸውን ነው። በእንዲህ አይነቱ አመራር ማንኛውም ዓይነት ብሔራዊ ጥቅም ይከበራል ብሎ ማመን መሳሳት ብቻ ሳይሆን አውቆ አጥፊነት ነው።




# 3. የባህር-በር ጥያቄን ለምን ዛሬ ማቅረብ ተፈለገ?

ጥያቄው እየቀረበ ያለው በአገር ጥቅም ስም ቢሆንም የጀርባ ዓላማው ግን ትኩረት ለመሳብና የስልጣን የበላይነትን የበለጠ ለማጠናከር መሆኑን መገንዘብ ጠቃሚ ይሆናል። በእኔ እይታ ጠቅላይ ሚኒስትሩ አስቀድሜ እንደጠበቅሁት በአሁኑ ወቅት አጀንዳውን ይዘው ብቅ ያሉት የተለያዩ የቅርብ፣ የመካከለኛና የሩቅ ጊዜ ፍላጎት ይዘው እንደሆነ መገመት ይቻላል።

## 3.1. ከቅርብ ጊዜ ፍላጎት አንጻር

ጠቅላይ ሚኒስትሩ፡-

- ከፕሪቶሪያው የሠላም ስምምነት በኋላ በኢትዮጵያዊውና በአማራው ብሔርተኛ ዘንድ ያጡትን ተቀባይነት እንደገና ለማግኘት፣ ይህንን ለማሳካትም ህዝቡ ትኩረቱን ከወቅቱ የአማራ ክልል ጦርነት ላይ እንዲያነሳና በዚህም ምክንያት ትግሉ ይዳከማል ብሎ በማሰብ፤
- ሻዕቢያን ለመበቀል በማሰብም የትግራይ ኃይሎች ተባባሪ ይሆኑኛል ብለው በመገመት፣
- የሳዑዲ አረቢያ ተቀናቃኝ ከሆነችው የአረብ ኤሚሬትስም በጦርነቱ ምክንያት የመሳሪያና የገንዘብ እርዳታ ላገኝ እችላለሁ ብለው በማሰብ፣
- ዓለም-አቀፍ ማህብረሰቡም አካባቢውን ወደ ባሰ ቀውስ ያስገባዋል ብሎ በመስጋት የተሻለ ትኩረት ሊሰጠኝና የማባባያ እርዳታና ብድርም ሊለግሰኝ ይችላል ብለው በመገመት፣
- እነዚህን ውጤቶች በማሳካትም የባህር-በር አጀንዳን በአንድ በኩል ተቃዋሚዎችን ለማዳከም፣ በሌላ በኩል ደግሞ በፓርቲዬና በህዝቡ ዘንድ የሚኖረኝን ማህበራዊ መሰረት ለማጠናከርና የስልጣን ዕድሜዬን ለማራዘም እጠቀምበታለሁ ብለው በማሰብ አጀንዳውን በአደባባይ ለማቅረብ እንደተገፋፉ መገመት ይቻላል።

## 3.2. ከመካከለኛ ጊዜ ፍላጎት አኳያ

ጠቅላይ ሚኒስትሩም ሆኑ አገሪቱ የመሰንበት እድሜ አግኝተው ለ2018 ዓ. ምህረቱ ምርጫ ከደረሱ፣ የባህር-በር ጥያቄን የምርጫ ዘመቻዬ ዋና አጀንዳ አድርጌ ምርጫውን ለማሸነፍ ልጠቀምበት እችላለሁ ብለው ሊያስቡ ይችላሉ። ምናልባትም ጦርነት ውስጥ ከገባሁ ከባድመ ጦርነት በኋላ የቀድሞው ወዳጄ አቶ ኢሳያስ እንዳደረጉት ሁሉንም የመብት ጥያቄ በጦርነት ሰበብ በማፈን ለረዥም ጊዜ በስልጣን ላይ የመቆየት ምኞቴን ለማሳካት እችላለሁ ብለው ሊያስቡም ይችላሉ።

## 3.3. ከረዥም ጊዜ ፍላጎት አኳያ

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ለረዥም ጊዜ ወይም እስከ ህይወታቸው ፍጻሜ ድረስ በስልጣን ንግስና ላይ የመቆየት የግብዝነት ፍላጎት ያላቸውና ለስም እና ለዝና አብዝተው




የሚጨነቁ ሰው ናቸው። ስለሆነም የህዳሴ ግድብን የግንባታ ታሪክ ከአቶ መለስ ዜናዊ ስም መነጠል የተሳናቸው ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ቀይ-ባህርን የታሪክ መዘከሪያዬ /Legacy/ ማድረግ አለብኝ ብለው ሊያስቡም ይችላሉ።

ለአለፉት 5 ዓመታት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ምን እንደሚያስቡ ብቻ ሳይሆን እንዴት እንደሚያስቡ በአግባቡ ለመገንዘብ ከቻልን የወቅቱ የባህር-በር ጥያቄ የተነሳው ከአገርና ከህዝብ ጥቅም አኳያ ሳይሆን ከእነዚህ የቅርብ፣ የመካከለኛና የሩቅ ጊዜ ፍላጎቶቻቸው አኳያ እንደሚሆን መገመት ቀላል ነው።

## 4. የወቅቱ የባህር-በር ጥያቄ ምን ውጤት ሊያስከትል ይችላል?

ይህንን ጥያቄ ተገቢ ከሆነ የፖለቲካ አመክንዮ አንጻር ልንመዝነው ከሞከርን - አሁን ላይ ያለው የኢትዮጵያ መንግሥትና ሰራዊት ከሚገኝበት የተዳከመ ሁኔታ፣ ከአገሪቱ የኢኮኖሚ ውድቀት፣ አገሪቱ ካለችበት የዲፕሎማሲ ጫና፣ እንዲሁም ጠቅላይ ሚኒስትሩ አሁን ላይ ከአላቸው ዝቅተኛ የህዝብ ተቀባይነትና አገሪቱ ከምትገኝበት የእርስ-በርስ ጦርነትና መከፋፈል አኳያ ትኩረት ለመሳብና ያልተገባ ተፅዕኖ ፈጣሪ ለመሆን ከመሞከር ባለፈ በባህር-በር ጥያቄ ምክንያት ወደ ጦርነት በመግባት ተጠቃሚ ሊሆኑ አይችሉም። ይሁንና ፖለቲካዊ አመክንዮን መመዘኛ በማድረግ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ወደ ጦርነት አይገቡም ብሎ በእርግጠኝነት መደምደም አይቻልም። የዓለምን የሠላም ኖቤል ከተሸለሙና "መግደል መሸነፍ ነው" የሚል ደፋር መፈክር በአሰሙን ማግስት አገሪቱን ወደለየለት የእርስ-በርስ ጦርነት ያስገቡት ጠቅላይ ሚኒስትር "ይህንንስ ሊያደርጉት አይችሉም" ተብሎ በእርግጠኝነት አይሆንም ሊባል የሚችል ምንም ዓይነት ግምት አይኖርም።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በምክንያት የሚያስቡ ቢሆን ኖሮ እስካሁንም በማያሸንፉት ጦርነት ውስጥ ደጋግመው ሲገቡ ባላየናቸው ነበር። አሁንም እጅግ በጣም ባነሰ ግምትም ቢሆን የስልጣን ዘመኔን የማራዝም ዕድል ይኖረኛል ብለው ካሰቡ በቀላሉና በጀብደኝነት ወደ ጦርነት ለመግባት ሊቋምጡ ይችላሉ። ነግር ግን ወደ ጦርነት ቢገቡ የአገዛዝ እድሜያቸውን የበለጠ ከማሳጠርና የአገሪቱን የመፍረስ ሂደት የበለጠ ከማፋጠን ባለፈ ጦርነቱን በድል ሊወጡትም ሆነ የአገሪቱን የባህር-በር የማግኘት ፍላጎት ሊያሳኩ አይችሉም። እዚህ ላይ ጦርነቱ ተካሂዶ ሲቻል የሁለቱን፣ ሲያንስ የአንዱን አምባገነን ዕድሜ ካሳጠረልን ቢካሄድ ምን ችግር አለው? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። በእኔ እምነት ግን የአምባገነን መሪዎችን ዕድሜ ለማሳጠር ተብሎ ወደ ከባድ ጦርነት መግባትና እንደገና የመቶ ሺህ የድሃ ልጆችን ህይወት ማጣት ኢ-ሞራላዊ የሆነ ወንጀል ነው።




ጠቅላይ ሚኒስትሩ ምንአልባት የአሜሪካኖችን ይሁንታ ካገኙ፣ የተባበሩት አረብ ኤሚሬትስ በሙሉ አቅሟ መሳሪያና ገንዘብ ከረዳቻቸው፣ የትግራይ ኃሎችም አቶ ኢሳያስን ለመበቀል ተገፋፍተው በሙሉ አቅማቸው ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጎን ከተሰለፉ ጦርነቱ ቢያንስ አቶ ኢሳያስን ከስልጣን የማስወገድ ውጤት ሊያስገኝ ይችላል።

ነገር ግን አሜሪካኖች የአቶ ኢሳያስን ከስልጣን መወገድ ሊፈልጉት ቢችሉም ጦርነቱ በምን ሁኔታ ሊጠናቀቅ እንደሚችል በርግጠኝነት ሊያውቁ ስለማይችሉና አካባቢውንም ወደ ባሰ ትርምስና ቀውስ ሊያስገባው ይችላል ብለው ስለሚሰጉ ጦርነቱ እንዲካሄድ ላይደግፉ ይችላሉ። ኤሚሬትስም ከሌላው ዓለም ሁሉ በተቃራኒ ቆማ በሙሉ አቅም የጠቅላይ ሚኒስትሩ አጋር ልትሆን የምትችልበት ዕድል ጠባብ ነው። የትግራይ ኃይሎችም ሻዕቢያ በህዝባቸው ላይ ካደረሰው አሰቃቂ በደል አኳያ ወደ ኤርትራ ለመዝመት ከፍተኛ ፍላጎት ሊኖራቸው ይችላል። ይሁንና የትግራይ ህዝብ ባለፈው ሁለት ዓመት ካሳለፈው መራር ሰቆቃ አኳያ ከጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ጎን ቁሞ ሊዋጋ ይችላል ብሎ መገመት አስቸጋሪ ይሆናል።

በእኔ እምነት የትግራይ ኃይሎች ከሁሉም ነገር በላይ ሻዕቢያን የመበቀሉ ፍላጎት በልጦባቸው ወይም ከጠላቶቻችን መካከል አንዱን እንቀንስ ብለው በማሰብ የጦርነቱ ተሳታፊ የሚሆኑ ከሆነውሳኔአቸው ሌላ ትልቅ ታሪካዊ ስህተት ይሆናል። በአሁኑ ወቅት ለትግራይም ሆነ ለአማራ ኃይሎች ከጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይና ከአቶ ኢሳያስ መካከል አንዱን መምረጥ የግድ አያስፈልጋቸውም። እንዲህ ዓይነቱ ምርጫም አትራፊ አያደርጋቸውም። ለእነሱ የሚዋጣው አማራጭ ሲቻል በጋራ ተባብሮ አገዛዙን መታገል፣ አለበዚያም ራስን ችሎ መቆም ነው። በነገራችን ላይ አንዳንድ የትግራይ አክራሪ ብሔርተኞችም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ወደ ስልጣን ከመጡ በኋላ ቀይ-ባህርን ታሳቢ ያደረገ የአዲስ አገር ፈጠራ ፍላጎት ማውጠንጠን እንደጀመሩም ልብ ማለትና ይህንንም ጉዳይ ከወቅቱ ሁኔታ ጋር ማገናዘብ ጠቃሚ ይሆናል።

እንኳንስ ወደ ሌላ አውዳሚ ጦርነት ውስጥ መግባትና ያለተገቢ ወቅትና ያለበቂ ዝግጅት በአሁኑ ወቅት የባህር-በር አጀንዳን በአደባባይ ማቀንቀናችን በራሱ ቀላል የማይባል ዋጋ ያስከፍለናል። ውስጣዊ ችግራችንን የበለጠ የማባባስ፣ ከጎረቤቶቻችን ጋር ያለንን አለመግባባት የበለጠ የማስፋት፣ በዓለም-አቀፍ ማህብረሰቡ ዘንድም እንደ ጠብ-አጫሪና በጥባጭ ተደርገን እንድንታይ ያደርገናል። በአጠቃላይ ላለፉት 5 ዓመታት ጠቅላይ ሚኒስትሩ የተቃዋሚ ፓርቲዎችን አጀንዳዎች ሁሉ እየኮረጁ፣ ነገር ግን በአግባቡ ሲፈጽሙት ሳይሆን አራክሰው ሲያስቀሩት እንዳየነው ሁሉ ይህንንም ስትራቴጅካዊ የሆነ የባህር-በር ታላቅ አጀንዳ በተመሳሳይ ሁኔታ ከማራከስና የበለጠ እንዲወሳሰብ ከማድረግ ባለፈ ለተጨባጭ ውጤት ሊያበቁት ይችላሉ የሚል እምነት የለኝም።

የጠቅላይ ሚኒስትሩ የባህር-በር ጥያቄ ከአሁን ቀደም ነዳጅ አወጣሁላችሁ፣ የተፈጥሮ ዝናብን የሚተካ ሰው-ሰራሽ ዝናብ አዘንብኩላችሁ፣ መረጃ የማሰባሰብ አቅማችንን የላቀ ደረጃ ላይ የሚያደርስ መንኮራኩር ወደ ጠረፍ አመጠቅሁላችሁ፣ የኮረና ቫይረስን መድሃኒት አገኘሁላችሁ፣ ስንዴ ኤክስፖርት በማድረግ ከተመጽዋችነት አወጣኋችሁ፣




በአንድ ዓመት 32 ቢሊዮን ችግኝ በመትከል የከባቢውን አየር ለወጥኩት፣ ከ30 ዓመት በኋላ በዓለም ከሚኖሩት ሁለት ሃያላን አገሮች ውስጥ ኢትዮጵያን አንዷ አደርጋታለሁ ወዘተ... በማለት የህልም እንጀራ ሲያበሉን ከከረሙት በተለየ በሠላምም ሆነ በጦርነት የኢትዮጵያን የባህር-በር ጥያቄ ሊያሳኩ የሚችሉ መሪ አይደሉም።

ከተደጋጋሚ ስህተት መማር ያለመቻል ዝግመት ከሌለብን በስተቀር - ከ1 ሚሊዮን በላይ የሆነ ህዝብ ፋይዳ በሌላው ጦርነት ያስፈጀ፣ ከ7.5 ሚሊዮን ህፃናት በላይ ከትምህርት ገበታ ውጭ ያደረገ፣ የአገሩን ግዛት የውጭ ኃይሎችን ጋብዞ ያስወረረ፣ ከ5 ሚሊዮን በላይ የሆነ ተፈናቃይና ከ25 ሚሊዮን በላይ የሆኑ ረሃብተኛ ዜጎች ባሉበት አገር ከወጪም ሆነ ከመጠን አኳያ ከአሜሪካኖቹ የኋይት ሃውስ ቤተ መንግሥት ከመቶ እጥፍ በላይ የሚሆን ቅንጡ የቤተ መንግሥት ከተማ በዚች ድሃ አገር ላይ የሚገነባን አንድ ግብዝ መሪ የባህር-በር ባለቤት ያደርገናል ወይስ አያደርገንም ብለን ለመዋያየት መሞከራችን በራሱ ኢትዮጵያውያን የምንገኝበትን የዝቅጠት ደረጃ የሚያሳይ ነው። ገና ምኑንም ሳይዙት በሌለ ባህር የባህር ኃይል ሠራዊት ማሰልጠን የጀመሩ ስሜታዊ መሪ የባህር-በር ፍላጎታችንን ያሳኩልናል ብሎ መመኘት "ላም አለኝ በሰማይ" አይነት ነው።

በአጠቃላይ ኢትዮጵያ የባህር-በር ጥያቄዋን ግልጽ የአደባባይ አጀንዳዋ አድርጋ ለማቀንቀን -በቅድሚያ ውስጣዊ እንድነቷን ማጠናከር፣ የአንድ ብሔር ሳይሆን የሁሉም የአገሪቱ ህዝብ ወኪልና ተቆርቋሪ የሆነ ጠንካራ መንግሥት ማግኘት፣ በየአቅጣጫው የመገንጠል ጥያቄ የማይነሳበትን ሁኔታ መፍጠር፣ በቅርብ ጎረቤቶቻችንና በዓለም-አቀፍ ማህበረሰቡ ዘንድ በቂ አክብሮትና ታማኝነት ያላት አገር መሆን ያስፈልጋል። አጀንዳውም የአጭር፣ የመካከለኛና የረዥም ጊዜ ዕቅድ ወጥቶለት፣ በጥናት ላይ የተመሰረተ ጠንካራ መዋቅራዊ ዝግጅት ተደርጎበት በጊዜያዊ ስሜትና የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ ሳይሆን በበሰለና በሰከነ መንገድ የህዝብና የትውልድ ጥያቄ ሆኖ መካሄድ አለበት።

የባህር-በር ለማግኘት የሚኖረን አጀንዳና አጀንዳውን ለማሳካት የምንከተለው ስልትም ጎረቤት አገሮችን ከጥቅም ልውውጥ አኳያ እኛ የበለጠ መጠቀም እንችላለን ብለው በማሰብ ከኛ ጋር ለመደራደር እንዲሽቀዳደሙ እንጂ ጥቅማችንን እናጣለን ብለው እንዲሰጉ የሚያደርግ መሆን የለበትም። በተለይም ከኤርትራ ህዝብ ጋር በተያያዘ የሚኖረን አቀራረብ በዚህ አግባብ የተቃኘ ሊሆን ይገባዋል። አጀንዳውን ለማሳካት ኤርትራ አንድ አማራጭ እንጂ ብቸኛ አማራጭ ተደርጋ መታዬትም የለባትም።






# መደምደሚያ

የባህር-በር ኢትዮጵያ ያለአግባብና በግፍ ያጣችው፣ ለወደፊት ህልውናዋ መቀጠልም አብዝቶ የሚያስፈልጋት ታላቅ አገራዊና ስትራቴጂካዊ አጀንዳዋ ነው። ይሁንና አሁን ላይ ከምትገኝበት እጅግ አሳሳቢ የሆነ የህልውና አደጋ አኳያ ቅድሚያ ልትሰጠው የሚገባ አጀንዳ አይደለም። ብዙ ዕዳ እየከፈለችም ቢሆን ኢትዮጵያ ያለባህር-በር ባለቤትነት ላለፉት 32 ዓመታት በኢኮኖሚ እያደገች ጭምር ህልውናዋን አስጠብቃ ኖራለች። የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አገዛዝ በስልጣን ላይ አስከቀጠለ ድረስ ግን ኢትዮጵያ ባህር-በር ቢኖራትም ባይኖራትም ህልውናዋ ከመጥፋት አይድንም።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ያለግጭትና ጦርነት መኖር እችላለሁ ብለው የማያምኑና የህዝብ ዕልቂት ከቁጥር የተለየ ትርጉምና ስሜት የማይሰጣቸው እልቂትን የተለማመዱ ሰው ናቸው። እርሳቸው በስልጣን ላይ እስካሉ ድረስ ከአንድ ጦርነት ወደሌላ ጦርነት ከመሸጋገርና መጨረሻ ላይም ደህይተንና እርስ-በረስ ተላልቀን አገራዊ ህልውናችንን ከማጣት የተለየ ሌላ ዕጣ-ፈንታ አይኖረንም።

በተገቢ ጊዜና ዝግጅት ያልቀረበ የባህር-በር ጥያቄ ወደ ሌላ የእልቂት አዙሪት ከማስገባትና የተያያዝነውን እየተገዳደሉ የመፈራረስ ሂደት የበለጠ ከማፋጠንና አይቀሬ ከማድረግ በስተቀር ሌላ የሚያስገኝልን ፋይዳ አይኖርም። ስለዚህ ያለጊዜውና ያለበቂ ዝግጅት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ የስልጣን ማጠናከሪያና ማራዘሚያነት ያለአግባብ እየተቀነቀነ ያለውን የባህር-በር ጥያቄ ካለመደገፍም በላይ ማውገዝ ያስፈልጋል። የወቅቱን የባህር-በር ጥያቄ ተከትሎ ሊመጣ የሚችለውን ጦርነትም በሙሉ ልብ ተባብረን ልንቃወመውና ልናስቀረው ይገባል።

አሁን ላይ ከሁሉም በላይ የሚያስፈልገን እርቅና ሠላም ነው እንጂ ሌላ አውዳሚ ጦርነት አይደለም። እንደ ህዝብና አገር በህልውና የመቀጠል ልባዊ ፍላጎት ካለን “ጦርነት ከእንግዲህ በቃን!” በማለት በጦርነትና በጦረኞች ላይ ማመፅ አለብን።

ዛሬ ላይ የብሔራዊ ደህንነታችን “ቁጥር አንድ ስጋት” የባህር-በር አለመኖር ሳይሆን የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ በስልጣን ላይ መቀጠል ነው። ስለሆነም የኢትዮጵያን ህልውና አስጠብቀን ለማስቀጠል ዛሬ ላይ በቀዳሚነት የሚያስፈልገን የባህር-በር ሳይሆን የጠቅላይ ሚኒስትሩ ከስልጣን መውረድ ነው። የባህር-በር የማግኘት ጥያቄ መጀመሪያ ከመፍረስ መዳናችንን ካረጋገጥንና እንደ አገርና ህዝብ በሁለት እግራችን ከቆምን በኋላ እንደርስበታለን። የዚያ ሰው ይበለን።

ልደቱ አያሌው

ጥቅምት 19 ቀን 2016 ዓ.ም